# Gender and Generations Ethiopia

Migrating out of Poverty

## የጥናት አጀንዳ

እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ በኢትዮጵያም ሆነ በዐለም አቀፍ ደረጃ በስደተኞች ጉዳይ ላይ ትኩረት ተደርጎ የቆየ ቢሆንም ስደት በስደተኞቹ ቤተሰቦች ላይ ስለሚኖረው ተጽዕኖ እምብዛም አልታወቀም፡፡ይህ የጥናት ፕሮጀክት ከስደት በመነጩ የምጣኔ ሀብት፣ ማህበራዊና ባህላዊ ለውጦች በስደተኛ ቤተሰቦች ትውልዳዊና ጾታዊ ግኑኝነትቶች ላይ የሚያሳድሩትን ተጽዕኖዎች ይመረምራል፡፡ በኢትዮጵያ የስደተኝነትን ፖለትካዊ ኤኮኖሚ በመተንተን፤ ፕሮጀክቱ የማህበራዊና ባህላዊ ለውጦች በስደተኝነት ላይ ተጽዕኖ እንዴት እንደሚፈጠሩና ስደተኝነት በበኩሉ በለውጦች ውጤቶች ላይ በስደተኛ ቤተሰቦች ውስጥ ተጽዕኖ እንዴት እንደሚያመጣ ይመለከታል፡፡ በተጨማሪም ፕሮጀክቱ በስደት ምክንያት የሚፈጠረው የሀብት ለውጥ በተለያዩ የቤተሰቡ አባላት ላይ እንዴት ተጽዕኖ እንደሚፈጥርና ይህ ምን ያህል በቤተሰብ ውስጥ ከሴቶች ተቀባይነት ጋር ግኑኝነት እንደሚኖረው ይመረምራል፡፡ በህብረተሰቡ ውስጥ በስደተኞች ቤተሰቦች ውስጥ ያለውን የማህበራዊ ግኑኝነት ደረጃዎችን ለመረዳት መረጃዎችን እንገነባለን፤ እንዲሁም ስደተኝነት ለስደተኞቹና ቤት ለቀሩ ቤተሰባቻቸው የሚሰጠውን ሃላፊነቶችና ነጻነቶች እንመረምራለን፡፡ ይህ በጾታዊና ትውልዳዊ መስተጋበር ላይ የሚደረግ ጥልቀት ያለው ትንታኔ ምን ምን ምክንያቶች በተወሰኑ የህብረተሰብ ክፍሎች ውስጥ ስደትን እንደሚያበረታቱና ስደተኝነት ባጭርና በረጅም ጊዜ ውስጥ የሚያስከትላቸውን ተጸዕኖዎችና ወደፊት ወደ ምን አይነት ሽግግር እንደሚያመራ ለማሳየት ይረዳናል፡፡

## መሠረታዊ የጥናቱ ጥያቄዎች

- ስደተኝነት በቤተሰብ ግንዛቤ ላይ እንዴት ተጽእኖ ያደርጋል?·ስደተኝነት፣ ጾታን መሠረት ያደረጉ ግኑኝነቶችና የአድራጊ የቦታዎች ለውጥን እንዴት ያስተጋብራል?
- በስደተኛ ህብረተሰብ ውስጥ ከስደት በሚገኘው ገቢ አጠቃቀም ላይ በቤተሰቡ ውስት ምን አይነት ጾታዊ አሰላለፍ ይታያል? ስደተኝነትን በተመለከተ በሀገር ውስጥ፣ ባለማቀፍ እንዲሁም በሀገር ውስጥና አለም አቀፍ ሰደተኝነት ደረጃ የቤተሰብ ተሳትፎ ልዩነት አለ?
- ምን አይነት የስደተኛ ቤተሰብ የአጭር ወይም የረጅም ጊዜ የኢንቨስትመንት እቅዶች አሉ? ከስደት ከሚገኘው ገቢ ጋር የተያያዙ ናቸው?
- ስደት በስደተኞች ቤተሰቦች ውስት የህይወት ምርጫ ላይ እንዴት ተጽዕኖ ያሰከትላል?

## የጥናቱ አላማዎች

የዚህ ፕሮጀክት አላማዎች በስደት፣በጾታ፣ በትዉልድና በድህነት መካከል ያሉትን ግኑኝነቶች በተመለከተ የተሻለ ግንዛቤ ማግኘት ነው፡፡ በስደተኝነት ላይ በማቶኮር ፕሮጀክቱ ረከስ ባሉ ስደቶች ወይም በቀላሉ ሊደረሱ የሚችሉትን እንዲሁም ወጪ የሚያስከትሉትንና የወረቀት ሥራዎችን የሚመለከቱትን እንዲሁም አስቸጋሪ ጉዞዎችን የሚያካትቱን ይፈትሻል፡፡

## የዚህ ጥናት ፕሮጀክት እምቅ አስተዋጽዖዎች

ይህ ጥናት UKAID ሰላማዊ የስደተኝነት መንገዶችን በማጠናከርና በማስፋፋት የስደተኞችንና የህብረተሰባቸውን ተጠቃሚነት በማሳደግ በአፍሪካ ውስጥ ቀጣይነት ያለውን እድገት ለማምጣት ያስችላል የሚላቸውን መንገዶች ይለያል፡፡ የዚህ ጥናት ግኝቶች በገጠሪቱ ኢትዮጵያ ጾታን መሰረት የደረገ እያደገ የመጣውን የለውጥ እንቅስቃሴዎችን በማስገንዘብ ስደተኝነት በተለያዩ የዕድሜ ክፍሎች ላይ የሚያሰከትለውን ተጽዕኖዎችን ያሳያል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ የዚህ ጥናት ግኝቶች ስደትን በተመለከተ ፖሊሲና ተግባራዊ ሥራዎችን ለሚሠሩት ለኢትዮጵያ መንግስትና ለሌሎች በስደት፣ ስርዐተ-ጾታ፣ በወጣቶችና በእድገት ጉዳዮች ላይ ለሚሠሩ ብሄራዊና አህጉራዊ ድርጅቶች ጠቃሚ ይሆናል፡፡

Organisation for Social Science Research in Eastern and Southern Africa (OSSREA)
Research Lead - Dr. Adamnesh Bogale
Email - info@ossrea.net
www.ossrea.net
migratingoutofpoverty.dfid.gov.uk
+251-11-1239484, P.O. Box 31971, Addis Ababa, Ethiopia

OSSREA
UKaid from the British people